የሰ/መ/ቁ. 59906

የካቲት 09 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት - ነገረ ፈጅ አቶ ፈለቀ እንግዳሸት ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ኃ/ማርያም ሻረው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር ክርክር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታውም የአሁን ተጠሪ የሥራ ውሉ ተቋርጦ እንዲሰናበት የተደረገው ከሕግ ውጭ ስለሆነ አሠሪው ድርጅት ወደ ሥራው እንዲመልሰው ይገባል፣ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጭ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅሞች ሊከፈሉት ይገባል በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/3/ መሠረት የቀረበ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በገደብ አሳሳ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሹ ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ ሆኖ ክሱ አሠሪው ድርጅት የሆነው የአሁኑ አመልካች ከሕግ ውጭ እኔን በወንጀል በመጠርጠር አግዶኝ እንዳልሠራ ስላደረገ ወደ ሥራ እንዲመለስ ይወስንልኝ በሚል የቀረበ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው ከሥራው እንዲታገድ የተደረገው የመንግሥት ቼክ በሀሰት ፈርሞ ከባንክ ገንዘብ ስላወጣ ነው፣ ከሥራ የሚያሰናብተው ከፍተኛ የዲሲፕሊን ጥፋት ስለፈፀመ የተወሰደው እርምጃ ትክክል ነው የሚል ክርክር ቢያቀርብም የወረዳው ፍ/ቤት ሠራተኛው በተጠረጠረበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በሕግ የተሰጠ ውሣኔ የለም፣ በመጠርጠሩ ብቻ ከሥራ ታግዷል የሚለው በሕጉ ተቀባይነት የለውም በማለት የአሁኑ አመልካች ሠራተኛውን ወደ ሥራው እንዲመልሰው፣ ደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅሞች ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊከፍለው ይገባል በሚል ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ የወረዳው ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን በየደረጃው ላሉ የኦሮሚያ ፍ/ቤቶች ቢያቀርብም ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች በ28/12/2002 በነገረ ፊጁ አማካኝነት በተጻፈ ማመልከቻ ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመባሉ ማመልከቻው ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት ተጠሪው በ23/03/2003 የተጻፈ መልስ ሲያቅርብ የአመልካች ነገረ ፈጅም የመልስ መልስ ሰጥቶበት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩም ተመርምሯል፡፡

አሠሪው ድርጅት የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበተው የድርጅቱን ቼክ በሀሰት በመፈረም ከባንክ ገንዘብ አውጥቶ በመውሰድ ከፍተኛ ጥፋት በመፈፀሙ ነው በማለት አጥብቆ የሚከራከር ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ከጥርጣሬ በቀር ወንጀሉን ስለመፈፀሜ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስላልቀረበ የአመልካች ክርክር በሕግ ተቀባይነት የለውም ባይ ነው፡፡

በመጀመሪያ ከሥራ ዕገዳ ሆኖ በመጨረሻ ከሥራ ስንብት ሆኗል የተባለው የአሁኑ አመልካች እርምጃ ከሕግ ውጭ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ዋናውን የክርክር ጭብጥ በተመለከተ ወረዳው ፍ/ቤት ሠራተኛው በወንጀል ተጠርጥሯል ከመባል በቀር በሕግ ጥፋተኛ ስለመሆኑ ተወስኖበት የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት ማስረጃው የፍርድ ቤት የወንጀል ውሣኔ ብቻ እንደሆነ አድርጐ በመውሰድ አሠሪው ሠራተኛው ፈጽሟል ስለሚለው ጥፋት በማስረጃ አላስረዳም ወደሚል ድምዳሜ ያመራ ሆኖ ይገኝ እንጂ አሠሪው ድርጅት ሠራተኛው ፈጽሟል ስለሚለው ጥፋት በፍርድ ቤት የተሰጠ የወንጀል ውሣኔ በማስረጃነት ማቅረብ ሣያስፈልግ የሰው ወይም ሌላ የጽሑፍ ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይችላል፡፡ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ጉዳዩ ተጣርቶ ከሥራ የሚያስወጣው ጥፋት ፈጽሟል የተባለበት የዲሲፕሊን ውሣኔ መኖሩ ከታወቀ በጽሑፍ ማስረጃነት የማይቀርብበት ምክንያት የለም፡፡ በወንጀል ምርመራ የተጣራበት ማስረጃም ካለ በማስረጃነት ቀርቦ ሊታይና ሊመዘን የሚችል ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች እነዚህን ሁሉ ማስረጃዎች እንዲያቀርብ አድርጐ አጣርቶ መወሰን ሲገባው ሠራተኛው በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ የተባለበት የፍርድ ቤት ውሣኔ በማስረጃነት ካልቀረበ ከሥራ የሚያሰናብተው ጥፋት ስለመፈፀሙ ማስረዳት እንደማይችል አድርጐ የወሰነው ትክክል አይደለም፡፡

ሌሎች ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተደርጐ ሣይጣራ የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

1. የገደብ አሳሳ ወረዳ ፍ/ቤት በፋይል ቁጥር 04168 በ23/09/2002 የሰጠው ብይን፣ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09309 በ30/10/2002 የሰጠው ትዕዛዝ እና

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 109450 በ13/12/2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል የገደብ አሳሳ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ ፈጽሟል ስለሚለው ጥፋት በፍርድ ላይ በተዘረዘረው መሠረት አሉኝ የሚላቸውን ሌሎች ማስረጃዎች እንዲያቀርብ አድርጎ በተገቢው መንገድ በማጣራት ከሥራ እገዳው ወይም ማሰናበቱ በሕጉ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም በሚለው ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ጉዳዩ ተመልሷል፡፡

2. የገደብ አሰሳ ወረዳ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ መሠረት እንዲፈጽም ታዟል፡፡
3. በዚህ መዝገበ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተጠሰው ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ